# ለመሪው የተሰጠ መመሪያ፡

- ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በዓለም ላይ በሰዎች ሕይወት ለሚደርስባቸው መከራዎች ሙሉ በሙሉ ምላሽ አይሰጥም፡፡
- በመከራ ውስጥ የሚያልፉትን ሰዎች ማጽናናት የምትችልባቸውን መንገዶች በዚህ ጥናት ትማራለህ፡፡
- መከራ ቢደርስብህ እንዴት ማለፍ እንደምትችል ራስህን ታዘጋጃለህ፡፡

ይህ ጥናት በቀዳሚነት በሶዶ ክርስቲያን ሆስፒታል ውስጥ በበሽታ ከሚማቅቁ ሰዎች ጋር የሚሰሩትን የሆስፒታል ሠራተኞች ለመርዳት የተዘጋጀው ነው፡፡ እኛም አማኞች እንደመሆናችን መጠን በሕይወታችን መከራና ፈተና ስለሚደርስብን ለእኛም ጭምር ይጠቅመናል፡፡
ሁሉም ሰው በዓለም ላይ መከራና ክፋት ለምን እንደሚከሰት ለማወቅ ተቸግሯል፡፡ በዓለም ላይ የሚከሰተውን ችግር በሙሉ እንድናውቅ መሠረት የሚሆነን የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ይሁን እንጂ በስቃይ ውስጥ ያሉ ሰዎች ርህራሄ እንደሚያስፈልጋቸው ማወቅ አለብን፡፡ ስቃያቸው እውነትን እንዳያወቁ ልቦናቸውን ሊያሳውር ይችላል፡፡ እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳላቸው ልናሳያቸውና ሰዎች ችግራቸው ምን እንደሆነ እንዲረዱ በመከራ ውስጥ ሊያልፉ እንደሚችሉ ማወቅ አለብን፡፡
<u>አንድ የተቸገረን ሰው ብታገኝ ቶሎ ብለህ ምክር ለመስጠትና ምላሽ ለመስጠት አትቸኩል፡፡</u> <u>በሞት ጥላ መካከል እንኳን ብናልፍ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ይሆናል፡፡</u> <u>በሌሎች ላይ ትዕግስት ሊኖረን ይገባል፡፡ ወደ ድል ጎዳና ለመድረስ ረጅም ጊዜ ሊወስድብን ይችላል፡፡</u>

አንድ ሰው ችግሩን በታማኝነት ሲያካፍል ሌላውም ለማካፈል ድፍረት ያገኛል፡፡ የቡድኑ አባላት በእነዚህ ስለ መከራ የተመለከቱ ጥያቄዎች ዙሪያ ግልጽ ውይይት የሚያደርጉበትን ቦታ መሪዎች ማመቻቸት አለባቸው፡፡

የሚከተሉት ሀሳቦች ለመሪዎች የሚጠቅሙ ናቸው፡-

1. ወደ ሳምንቱ የቡድን መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ከመምጣትህ በፊት በግልህ ተዘጋጅተህ ና፡፡ ይህን ማድረግ ለጥያቄዎቹ ቅድመህ ዝግጅት እንዲታደርግ ይረዳሃል፡፡
2. እያንዳንዱን <u>ደረጃ</u> በቅደም ተከተል <u>አድርግ</u>፡፡
3. ትምህርቶቹ እንድታነባቸውና በውስጣቸው ያሉትን ቁልፍ ቃላት እንድትፈልግ ይጠይቁሃል፡፡ እንደታዘዝከው በቃላቱ ላይ ምልክት አድርግ፡፡ አልፎ አልፎ ክፍሎችን ደግመህ እንድታነባቸውና ሌሎች ቃላትን እንድትፈልግ ትጠየቃለህ፡፡ ደግመህ ደጋግመህ ለማንበብ ጊዜ ሊወስድብህ ይችላል፡፡ ግን ስለ ክፍሉ የጠለቀ መረዳት ይኖራሃል፡፡
4. የውይይት ጥያቄዎቹ የክፍሉን ዋና ሀሳብ ለማግኘት የሚመሩ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ከክፍሉ ጋር የሚገናኙ ሌሎች ተጨማሪ ጥያቄዎችን መጠየቅ ትችላለህ፡፡ እያንዳንዱ አባል በውይይቱ እንዲሳተፍ አበረታታ፡፡ ይህም በክፍሉ ላይ የበለጠ መረዳት እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋል፡፡
5. ከክፍሉ ሀሳብና ክፍሉ ለማስተላለፍ ከፈለገው ሀሳብ እንዳትወጣ ተጠንቀቅ፡፡ በሕይወታችን የተለማመድናቸው የተለያዩ ልማዶች እኛን ወደተሳሳተ መንገድ ሊመሩን ይችላሉ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ሁል ጊዜ ተቆጣጣሪያችን ነው፡፡

## ትምህርት-1

ደረጃ-1

**መግቢያውን አንብብ፡-** በዓለም ላይ መከራ ያለው ለምንድነው? አማኞች ለምን መከራን ይቀበላሉ? እግዚአብሔር የፈጠረው ዓለም መልካም እንደሆነ፣እግዚአብሔር ራሱ መልካም እንደሆነ እናምናለን፡፡ ታዲያ በዓለም ላይ ያለው ክፋት ምንጩ ምንድነው? የመጀመሪያው ምላሽ በዘፍጥረት መጽሐፍ ላይ አለ፡፡ ዘፍጥረት ስለ አዳምና ሔዋን ታሪክ ይናገራል፡፡ እነርሱ እግዚአብሔርን ያለመታዘዛው ዋጋ ነው፡፡ ሞትን እንደሚሞቱ እግዚአብሔር አስጠንቅቋቸው ነበር፡፡ መከራ፣ሞትና ሐጢአት ወደ ዓለም የመጣው የሰው ልጅ ባለመታዘዙ ምክንያት ሲሆን ዓለም ቀድሞ መልካም እንደነበረ መቀጠል አልቻለም፡፡

ደረጃ-2

ሮሜ፡8፡20-23 ያለውን ክፍል አንብብና ፍጥረት በሚለው ቃል ሥር አሥምርበት፡፡

‹‹ፍጥረት ለከንቱ ተገዝቶአልና በተስፋ ስላስገዛው ነው እንጂ በፈቃዱ አይደለም፤ ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሞሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ ነው፡፡ ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና፡፡ እርሱም ብቻ አይደለም ነገር ግን የመንፈስ በኩራት ያለን ራሳችን ደግሞየሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነት እየተጠባበቅን ራሳችን በውስጣችን እንቃትታለን፡፡››

ደረጃ-3

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. ከሥር ያሰመርከውን ‹‹ፍጥረት›› የሚለውን ቃል እንደገና ተመልከት፡፡ ፍጥረት የሚለው ቃል እንስሳትን፣እፁዋትን፣ተራሮችንና በእግዚአብሔር የተፈጠሩ ፍጥረታትን በሙሉ ያካትታል፡፡ ከዚህ የምትማረው ምንድነው? ፍጥረት በምን ዓይነት መንገዶች መከራን እንደሚቀበል ተወያዩ፡፡ ዓለም ሊበሰብስ በእሥራት ውስጥ አለ የምንለው እንዴት ነው?
2. ስለ ሰው ልጅ የምትማረው ምንድነው?
3. ፍጥረትና አማኞች ነፃ የሚወጡት መቼ ነው? ሰውነታችን የሚበዠው መቼ ነው? ራዕ፡21፡1-7 ያለውን ክፍል አንብብ፡፡
4. ይህ ዓለም መከራ የሞላበት ስለመሆኑ የተማርከው ነገር ምንድነው?

ደረጃ-4

2ጢሞ፡3፡1-5 ያለውን ክፍል አንብብና በዚህ ዘመን ስላሉ ሰዎች የሚገልጸውን ክፍል ዘርዝር፡፡

ቁ.1 ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ፡፡ ቁ.2 ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና ገንዘብን የሚወዱ ትምክህተኞች ትዕቢተኞች ተሳዳቢዎች ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ የማያመሰግኑ ቁ.3 ቅድስና የሌላቸው ፍቅር

የሌላቸው ዕርቅን የማይሰሙ ሐሜተኞች ራሳችውን የማይገዙ ጨካኞች መልካም የሆነውን የማይወዱ ቁ.4 ከዳተኞች፣ችኩሎች፣ በትዕቢት የተነፉ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ ቁ.5 የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ፡፡

የውይይት ሀሳቦች፡- በዚህ ዘመን ስላሉ ሰዎች ከዘረዘርካቸው ነገሮች የምትማረው ምንድነው ለችግርና ለመከራ ዋነኛ ምክንያት የሆነው ምንድነው

ደረጃ-5

ያዕቆ፡1፡2-5 ያለውን ክፍል አንብብና ስለ አማኞች በሚናገሩ ቃላት ከሥር አስምርባቸው፡፡
‹‹እንዲ----፣ ዘንድ›› የሚሉትን ቃላት በሳጥን ምልክ ውስጥ አስቀምጥ፡፡

ቁ.2-3 ወንድሞቼ ሆይ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት ቁ.4 ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም፡፡ ቁ.5 ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን ለእርሱም ይሰጠዋል፡፡

ደረጃ-6

**የውይይት ጥያቄዎች፡**

1. ስለ አማኞች የምትማረው ምንድነው? በሕይወታቸው የሚሆነው ምንድነው?
2. የእምነትህ መፈተን የሚያመጣው ውጤት ምንድነው?
3. በቁ.4 ላይ ‹‹ዘንድ›› የሚለውን ቃል ተመልከት፡፡ የፈተና ዓላማው ምንድነው?
4. ፈተና ለምን እንደሚደርስብህ ካላወቅህ ምን ማድረግ አለብህ? ቁ.5

የሚከተለውን ሀሳብ አንብብ፡- ለተስፋና ለብርታት የሚሆን የመጨረሻው ጥቅስ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡ ይህንን በቃልህ አጥናው፡- ‹‹አምላካችን መጠጊያችንና ኃይላችን ባገኘን በታላቅ መከራም ረዳታችን ነው›› መዝ፡(46)፡1

## ትምህርት-2

**እያንዳንዱን ደረጃ በቅደም ተከተል አድርግ፡፡**

ደረጃ-1

**መግቢያውን አንብብ፡-** በብሉይ ኪዳን ዘመን ኢዮብ በታላቅ መከራ ውስጥ አልፎ ነበር፡፡ ሦስቱ ወዳጆቹ ሊያጽናኑት መጥተው ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች ለኢዮብ የተናገሩት በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት እውነት ናቸው፡፡ ግን በሕይወቱ ጋር የሚዛመዱ አልነበሩም፡፡ እግዚአብሔር በእነዚህ ሦስቱ ሰዎች ደስ አልተሰኘም፡፡ እኛም ዛሬ ከዚህ ታሪክ ማለት ያለብንና ማለት የሌለብንን ነገሮች ተምረናል፡፡

ደረጃ-2

ከዚህ በታች የተጻፈውን ኢዮ፡1፡6-12 ያለውን ክፍል አንብብ፡፡ የእግዚአብሔርን ስም የሚጠቅሱትን ቃላት በሦስት ማዕዘን (Triangle) ምልክት ውስጥ አስቀምጥ፡፡ ስለ ሰይጣን የሚናገረውን ቃል አክብብ፡፡ ስለ ኢዮብ በሚናገረው ከሥር አስምር፡፡

ቁ.6 ከዕለታት አንድ ቀን እንዲህ ሆነ የአምላክ ልጆች በእግአብሔር ፊት ለመቆም መጡ ሰይጣንም ደግሞ በመካከላቸው መጣ፡፡ ቁ.7 እግዚአብሔርም ሰይጣንን፡- ከወዴት መጣህ? አለው፡፡ ሰይጣንም፡- ምድርን ሁሉ ዞርሁአት በእርስዋም ተመላለስሁ ብሎ ለእግዚአብሔር መለሰ፡፡ ቁ.8 እግዚአብሔርም ሰይጣንን፡- በውኑ ባሪያዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን እግዚአብሔርንም የሚፈራ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም አለው፡፡ ቁ.9 ሰይጣንም ለእግዚአብሔር እንዲህ ብሎ መለሰለት፡- በውኑ ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራው በከንቱ ነውን? ቁ.10 እርሱንና ቤቱን በዙሪያውም ያሉትን ሁሉ አላጠርህለትምን የእጁን ሥራ ባርከህለታል ከብቱም በምድር ላይ በዝቶአል፡፡ ቁ.11 ነገር ግን እጅህን ዘርግተህ ያለውን ሁሉ ዳብስ በእውነት በፊትህ ይሰድብሃል፡፡ ቁ.12 እግዚአብሔር ሰይጣንን፡- እነሆ ለእርሱ ያለው ሁሉ በእጅህ ነው ነገር ግን በእርሱ ላይ እጅህን አትዘርጋ አለው፡፡ ሰይጣንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ፡፡

ደረጃ-3

የውይይት ጥያቄዎች፡

1. ስለ ኢዮብ የምትማረው ምንድነው? በኢዮብ ላይ መከራ የደረሰው እርሱ ሐጢአት ስለ ሠራ ነው?
2. ስለ ሰይጣን የምትማረው ምንድነው? ኢዮብ መከራ ቢደርስበት እግዚአብሔርን ምን እንደሚል ነው ሰይጣን የጠበቀው? ቁ.11
3. ከዚህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔር የምትማረው ምንድነው?
4. ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚያገለግለው ስለተባረከ ብቻ እንደሆነ ሰይጣን አሰበ ቁ.9፡፡ ሰዎች የተናገሩትን የሚከተሉትን ዓ.ነገሮች አንብብ፡- ሰይጣን ልክ ነው ወይስ በእነዚህ ሰዎች አስተሳሰብ ላይ የነበረው ችግር ምንድነው? የሰዎቹ አስተሳሰብ ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡
   ሀ. ለምንድነው እግዚአብሔርን ያገለገልኩት? ብዙ ችግር ደርሶብኛል፡፡
   ለ. እግዚአብሔር ባለፀጋ አምላክ ነው:: ታዲያ እርሱን እያገለገልኩ ለምን ድሃ እሆናለሁ?
   ሐ. ስለ መከራ መስማትም አልፈልግም፡፡ እግዚአብሔር እንዲባርከኝ እፈልጋለሁ፡፡

ደረጃ-4

የሚከተለውን አንብብ፡- ለሚደርስብን ክፋትና መከራ እንደ ኢዮብ ሁል ጊዜ መልካም ምላሽ እናገኛለን ብለን መጠበቅ አንችልም፡፡ የታሪኩ ዋና ሀሳብ በመከራው ሰዓት በእግዚአብሔር ላይ ስለታመነው ኢዮብ እምነት ነው፡፡ ኢዮብ ልጆቹን፣ሎሌዎቹን፣እንስሳቱን፣ጤናውንና መልካም እድሉን በሙሉ አጣ፡፡ ኢዮ፡ 1፡20-22 ያለውን ክፍል አንብብና ኢዮብ በመለሰው ምላሽ ላይ ውይይት አድርግ፡፡

ቁ.20 ‹‹ኢዮብም ተነሣ መጎናጸፊያውንም ቀደደ፤ራሱንም ተላጨ፤ በምድርም ላይ ተደፍቶ ሰገደ፡፡ ቁ.21 እንዲህም አለ፦ ራቁቴን ከእናቴ ማሕፀን ወጥታቻለሁ ራቁቴንም ወደዚያ እመለሳለሁ፤ ***እግዚአብሔር*** ሰጠ፣***እግዚአብሔርም*** ነሣ፤ ***የእግዚአብሔር*** ስም የተባረከ ይሁን፡፡ ቁ.22 በዚህ ሁሉ ኢዮብ አልበደለም፤ ለእግዚአብሔርም ስንፍናን አልሰጠም፡፡›› እግዚአብሔር ዛሬ አንተን በግልህ የሚያስተምረው ምንድነው?

## ትምህርት-3

ደረጃ-1

***መግቢያውን አንብብ፦*** የአንድ ልጅ መጥፋት በዚህ ዓለም ካሉ ታላላቅ ስቃዮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ እንደዚሁም ሀብትህን ማጣት ትልቅ ሐዘን ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሰው ኢዮብ እንዴት ይሰቃይ እንደነበረ አስብ፡፡ ኢዮብ በራሱ ላይ ምን እየሆነ እንዳለ አልገባውም፡፡ በራሱ ላይ እየደረሰ ያለው መከራ በምን ምክንያት እንደሆነ ራሱን ሳይጠይቅ አይቀርም፡፡ ደግሞም ለምን ያህል ጊዜ እንደሚሰቃይ አያውቅም፡፡ ምንም እንኳን ይህ መከራ በእርሱ ላይ የደረሰበትን ምክንያት ባያውቅም ኢዮብ ግን እምነቱን በታላቁ እግዚአብሔር ላይ ጥሎ ነበር፡፡ በአፍቃሪው እግዚአብሔር ይደገፍ ነበር፡፡ የሚከተለው ታሪክ በመከራ ውስጥ የሚያልፉትን ሰዎች የምናጽናናባቸውን አዎንታዊ (ጥሩ) ና አሉታዊ (መጥፎ) መንገዶችን ያስተምረናል፡፡ የሚከተለውን ታሪክ አንብብና ከክፍሉ የምትማረውን እውነት ከቡድንህ አባላት ጋር ተወያይ፡፡

ኢዮ፡2፡9-13 ያለውን ክፍል አንብብና ሰዎች ኢዮብን ለማጽናናት ያደረጓቸውን ነገሮች ከሥር አስምርባቸው፡፡
ቁ.9 ላይ ሚስቱ፡-‹‹ እስከ አሁን ፍጹምነትህን ይዘሃልን? እግዚአብሔርን ስደብናሙት›› አለችው፡፡
ቁ.10 እርሱ ግን፡- ‹‹ አንቺ ከሰነፎች ሴቶች እንደ አንዲቱ ተናገርሽ ከእግዚአብሔር እጅ መልካሙን ተቀበልን፤ ክፉ ነገርንስ አንቀበልም?›› አላት፡፡
ቁ.11 ምስቱም የኢዮብ ወዳጆች ይህ የደረሰበትን ክፉ ነገር ሁሉ ሰምተው ከየአገራቸው መጡ እነርሱም ቴማናዊው ኤልፋዝ ሹሐዊው በልዳዶስ ነዕማታዊው ሶፋር ነበሩ፡፡ እነርሱም ሊያዝኑለትና ሊያጽናኑት በአንድነት ወደ እርሱ ለመምጣት ተስማሙ፡፡ ከሩቅም ሆነው ዓይናቸውን ባነሱ ጊዜ አላወቁትም፡፡ ድምፃቸውንም አሰምተው አለቀሱ፤ እያንዳንዳቸውም መጎናጸፍያቸውን ቀደዱ፤ ወደ ላይም በራሳቸው ላይ ትብያ ነሰነሱ፡፡
ቁ.13 ሰባት ቀንና ሰባት ሌሊትም ከእርሱ ጋር በምድር ተቀመጡ፤ ሕመሙም እጅግ እንደበዛ አይተዋልና ከእነርሱ አንድ ቃል የሚናገረው አልነበረም፡፡

ሰውን የማጽናኛ መንገድ እንደዚህ መሆን እንደሌለበት ከኢዮብ ሚስት የምንማረው ምንድነው?
ሌሎችን እንዴት ማጽናናት እንዳለብን ከኢዮብ ጓደኞች ሕይወት የምንማረው ምንድነው? እነርሱ ያደረጓቸውን ነገሮች ዘርዝር፡፡

ደረጃ-2

የሚከተለውን አንብብ፡- እግዚአብሔር ኢዮብን ቅን ሰው ብሎ ቢጠራውም ኢዮብ ግን መከራ አልተለየውም፡፡ እግዚአብሔር የአንድን ሰው እምነት ለመፈተን ሲፈልግ ሰይጣን በዛ ሰው ላይ መከራ ሲያመጣበት ዝም ይላል፡፡ የኢዮብ ጓደኞች በመጀመሪያ ትክክል የሆነው ነገር አደረጉ፡- ከኢዮብ ጋር አብረው ቁጭ በማለት ርህራሄአቸውን አሳዮት፡፡ ይሁን እንጂ በማስከተል በኢዮብ ላይ እየደረሰበት ያለው መከራ በምን ምክንያት እንደሆነ አንድ በአንድ ለእርሱ ይናገሩ ነበር፡፡ በኢዮብ ላይ በመፍረድ ምክርን ይለግሱለት ነበር፡፡ እነርሱ ለኢዮብ ታማኝ ነበሩ፡፡ ግን በእርሱ ላይ እየደረሰ ያለው ምን እንደሆነ አላወቁም፡፡ በኂላ እግዚአብሔር በእነዚህ በሦስቱ ሰዎች ደስ እንዳልተሰኘ እንማራለን፡፡ አሁን እነርሱ ለኢዮብ የለገሱለትን ምክር ተመልከትና እነርሱ ከሰጡት ምክር ውስጥ የትኛው መጥፎና የትኛው መልካም እንደሆነ እይ፡፡ የመጀመሪያው ቴማናዊው ኤልፋዝ ነበር፡፡ ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ልዩ መልዕክትና ራዕይ እንደተቀበለ ይናገር ነበር፡፡ ይህ አባባል ከዘመኑ ነቢያት አባባል ጋር ይመሳሰላል፡፡ እርሱ ለኢዮብ ያለውን ሀሳብ ጠቅለል አድርጎ የሚይዘውን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ክፍል አንብብ፡፡

4፡7-8 እባክህ አስብ፣ ንጹሕ ሆኖ የጠፋ ማን ነው? ከልበ ቅንስ የተደመሰሰ ማን ነው? እኔ እንዳየሁ ሐጢአትን የሚያርሱ መከራንም የሚዘሩ ይህንኑ ያጭዳሉ፡፡
5፡17 እነሆ እግዚአብሔር የሚገሥጸው ሰው ምስጉን ነው፡፡ ስለዚህ ሁሉን የሚችለውን የአምላክን ተግሣጽ አትናቅ፡፡ ቁ.18 እርሱ ይሰብራል፤ይጠግንማል፤ ያቆስላል፤ እጆቹም ይፈውሳሉ፡፡
5፡20 በራብ ጊዜ ከሞት በሰልፍም ከሰይፍ እጅ ያድንሃል፡፡

ኤልፋዝ ያለው ነገር እውነት ነው ወይስ ውሸት ነው? በኢዮብ ላይ መከራ እየደረሰበት ያለው እርሱ ሐጢአት ስለሠራና እግዚአብሔር እየቀጣው ስለሆነ ነው?

በልዳዶስ የተባለው ሌላኛው የኢዮብ ወዳጅ እርሱ እየተቀጣ ያለው በሐጢአት ምክንያት እንደሆነ ያስባል፡፡ ደግሞም ኢዮብ ቅን እንደሆነ ይህ ሰው ያስባል፡፡

8፡4-6 ልጆችህ በድለውት እንደ ሆነ እርሱ በበደላቸው እጅ ጥሎአቸዋል፡፡ እግዚአብሔርን ብትገሠግሥ ሁሉንም የሚችለውን አምላክ ብትለምን ንጹሕና ቅን ብትሆን በእውነት አሁን ስለ አንተ ይነቃል፤ የጽድቅህንም መኖሪያ ያከናውንልሃል፡፡

8፡13 እግዚአብሔርን የሚረሱ ሁሉ ፍጻሜአቸው እንዲሁ ነው፤ የዝንጉም ሰው ተስፋ ይጠፋል፡፡ (ኢዮብ በእውነቱ እግዚአብሔርን ረስቶት ነበር? በልዳዶስ የሚያወራው እውነት ነው?)

ሶፋር ጭካኔ የሞላበት ሰው ሲሆን ኢዮብን ውሸታም ይለዋል፡፡

ኢዮ፡11፡4 እና 11 አንተ፡- ትምህርቴ የተጣራ ነው በዓይንህም ፊት ንጹሕ ነኝ ትላለህ፡፡ ቁ.11 ምናምንቴዎችን ያውቃል፤ በደልንም ሲያይ ዝም ብሎ አይመለከትም፡፡

ከዚህ በታች እነዚህ ሰዎች የተናገሩትን ሀሳቦች በጥንቃቄ ተመልከትና እውነት ወይም ሐሰት መሆናቸውን ተናገር፡፡

1. እነዚህ ሰዎች በኢዮብ ላይ ፈርደውበት ንስሐ መግባት አለበት ይላሉ፡፡
2. እነዚህ ወዳጆች ኢዮብን በቃላቸው ረዱት፡፡
3. ከእነዚህ ሰዎች አንዱ በእግዚአብሔር ስም ይናገራል፡፡
4. አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ከሐጢአታቸው የተነሣ መከራን ይቀበላሉ፡፡

ደረጃ-3

እነዚህ ሦስቱ ሰዎች በአፍቃሪውና ቅን ፈራጅ በሆነው በእግዚአብሔር አመኑ፡፡ እውነት ነው እግዚአብሔር ቅን ፈራጅና አፍቃሪ አምላክ ነው፡፡ ይሁን እንጂ መልካም የሆኑ ሰዎች ሁሉ እንደሚበለጽጉና ክፉን የሚያደርጉ ሰዎች ሁሉ መከራን እንደሚቀበሉ የራሳቸውን ምክንያት ይሰጡ ነበር፡፡ ስለዚህ መከራ በሰዎች ላይ የሚደርሰው በተደበቀው ሐጢአት ምክንያት እንደሆነ አሰቡ፡፡

እርግጥ ነው መጽሐፍ ቅዱስ በሐጢአት ምክንያት ስለሚመጡ መከራዎች ምሳሌዎችን ይሰጣል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ በኢዮብ ላይ የሚፈርዱ ሰዎች እግዚአብሔርን አላስደሰቱትም፤ምክንያቱም በኢዮብ ላይ የሚደርሰው መከራ በሐጢአት ምክንያት አይደለም፡፡ እነዚህ ሰዎች ኢዮብን ከመርዳት ይልቅ ጭንቀቱን አባባሱበት፡፡

በኢዮ፡42፡7 ባለው ክፍል እግዚአብሔር ስለ እነዚህ ሦስቱ ሰዎች የሚናገረውን አንብብ፡፡

‹‹እግዚአብሔርም ይህን ቃል ለኢዮብ ከተናገረ በኋላ እግዚአብሔር ቴማናዊውን ኤልፋዝን፦ እንደ ባሪያዮ እንደ ኢዮብ ቅንን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና ቁጣዬ በአንተና በሁለቱ ባልንጀሮችህ ላይ ነድዶአል፡፡››

***ከዚህ ክፍል እኛ የምንማረው አንድ ሰው መከራን የሚቀበለው በዚህ በዚህ ምክንያት ነው ብሎ ለመናገር አለመቻል ወይም በድፍረት አለመናገር ነው፡፡ በእግዚአብሔር ስም ስትናገር በጣም መጠንቀቅ አለብህ፡፡ ምስጢሩን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ እርሱ ለባለቤቱ ይገልጥለታል፡፡***

ደረጃ-4

እኛ የምንማረው ምንድነው የመወያያ ነጥቦች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡ ይህ ሁለት ሳምንትና ከዛ በላይ ሊወስድ ይችላል፡፡

1. ኢዮብ ቅንና እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ቢሆንም መከራን ተቀብሏል፡፡
2. እኛ ለምን መከራን እንደምንቀበል  እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ምክንያቱን አይነግረንም፡፡
3. በሌሎች ሰዎችም ላይ መከራ ለምን እንደሚደርስ በእርግጠኝነት ማወቅ አትችልም፡፡ ኢዮ፡42፡3 ‹‹ያለ እውቀት ምክርን የሚሰውር ማነው?››
4. አንድ መከራ እየደረሰበት ያለውን ሰው ሐጢአት ስለሠራ ነው መከራ እየደረሰበት ያለው ብለህ ካሰብክ ያን ሰው ስታናግረው በጣም መጠንቀቅ አለብህ፡፡ መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው ያን ሰው ሐጢአቱን ሊያሳይ የሚችለው፡፡ (ዮሐ፡16፡8 እና ያዕ፡15) ኢትዮጵያዊያን አንድ መከራ እየደረሰበት ያለውን ሰው ሲያዩ ምን ይላሉ ወይም ምን ዓይነት ባሕሪይ ያሳዩአቸዋል?

5. ከዚህ ቀጥሎ ኢዮብ ለወዳጆቹ ስለነገረው ምክር ተወያዩበት፡፡ ‹‹ሁሉን የሚችለውን የአምላክን መፍራት ለሚተው ለመዛል ለቀረበው ስንኳ ወዳጁ ቸርነትን ሊያሳይ ይገባል፡፡ (ኢዮ፡6፡14) አንድ ተስፋ ለቆረጠው ሰው እንዴት ቸርነትን ልታሳይ ትችላለህ
6. በእኛ ላይ ለሚደርስብን ለማንኛውም ነገር የበላይ ተቆጣጣሪ የሆነው እግዚአብሔር አለ፡፡ ይህንን እውነት ሌሎች እንዲረዱ እንዴት መርዳት እንችላለን
7. አንድ በመከራ ውስጥ ያለውን ሰው ለማጽናናት ብንሄድ ለዛ ሰው ያለን አመለካከት እንዴት መሆን አለበት
8. መከራ በእኛ ላይ ለምን እንደሚደርስ ባይገባንም ችግር የለም፡፡ ኢዮብ በስሜት ውስጥ እየገባ ነው፡፡ ኢዮብ ማማረርና መበሳጨት አልፎም ሞትን ይመኝ ነበር፡፡ አሁን የኢዮብ ሕይወት ተበላሽቷል፤ እግዚአብሔርም የራቀውና ዝም ያለው ይመስላል፡፡ ከእምነቱ ጋር ይታገላል፤ነገር ግን እግዚአብሔርን አልካደውም፡፡ ኢዮ፡13፡15 ‹‹እነሆ ቢገድለኝ ስንኳ እርሱን በትዕግስት እጠባበቃለሁ፡፡››

## ትምህርት-4

ደረጃ-1

***መግቢያውን አንብብ፡-*** የኢዮብን መከራ ታሪክ ለመረዳት ትልቅ ተግዳሮት ነው የሚሆነው፡፡ እግዚአብሔር ወደ ኢዮብ መጣ፡፡ ነገር ግን የመከራውን መንስኤ አይነግረውም፡፡ ኢዮብ እንደዚህ አለ፡- ‹‹ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፤ በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ፡፡›› ኢዮብ በእግዚአብሔር ፊት ራሱን አዋረደ፡፡ ከዚህ በኋላ በሽታው ከላዮ ላይ ረገፈ፡፡ አሁን ኢዮብ አዲስ ቤተሰብና አዲስ ብልጽግናን ከእግዚአብሔር ዘንድ አገኘ፡፡ የኢዮብ ስቃይ ብዙ ከመሆኑ የተነሣ የእግዚአብሔርን ፈውስና እግዚአብሔር ለእርሱ ያሳየውን ርህራሄና ምህረት ለመለማመድ ጊዜ ወሰደበት፡፡ በመጀመሪያ ቀድሞ የደረሰበት ሀዘን በኋላ ከመጣው መልካም ነገር ሁሉ እንደሚበልጥ ተሰምቶት ሊሆን ይችላል፡፡

**የኢዮብን ታሪክ ወስደን ለራሳችን ሕይወት ትርጓሜ እንዳንሰጥና ከሕይወታችን ጋር እንዳናዛምድ በጣም መጠንቀቅ አለብን፡፡**

ይህ ታሪክ ኢዮብ የተባለው ሰው ታሪክ ነው፡፡ እንደዚሁም እያንዳንዱ አማኝ የራሱ የሆነ ታሪክ አለው፡፡ እግዚአብሔር ኢዮብን እንደገና ሊባርከው የገባለት ተስፋ ቃል እኛ ሁላችን እንደ ኢዮብ በልጆች፣በገንዘብ፣በብልጽግና ወይም በጤና እንድንባረክ የተገባልን ተስፋ ቃል አይደለም፡፡ ለኢዮብ የተሰጠው ዳግመኛ በረከት እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ ሆኖ ባይሰጠን በእግዚአብሔር ላይ እንቆጣለን፤ አልፎም በእርሱ መልካምነት ላይ ጥርጣሬ ያድርብናል ማለት ነው፡፡ በኢዲስ ኪዳን በያዕቆብ መጽሐፍ ላይ ኢዮብ የብልጽግና ሳይሆን የትዕግሥት አርአያ ሆኖ ተገልጹዋል፡፡

ያዕቆ፡5፡7-11 ያለውን ክፍል አንብብና ትዕግሥት የሚለውን ቃል ፈልግና ከሥሩ አስምርበት፡፡

> ቁ.7 እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ታገሡ፡፡ እነሆ ገበሬው የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ እስኪቀበል ድረስ እርሱን እየታገሠ የከበረውን የመሬት ፍሬ ይጠብቃል፡፡ ቁ.8 እናንተ ደግሞ ታገሡ ልባችሁንም አጽኑ የጌታ መምጣት ቀርቦአልና፡፡ ቁ.9 ወንድሞች ሆይ እንዳይፈረድባችሁ እርስ በርሳችሁ አታጉረምርሙ፤እነሆ ፈራጅ በደጅ ፊት ቆሞአል፡፡ ቁ.10 ወንድሞች ሆይ የመከራና የትዕግሥት ምሳሌ የሆኑትን በጌታ ስም የተናገሩትን ነቢያትን ተመልከቱ፡፡ ቁ.11 እነሆ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንችላዋለን፤ ኢዮብ እንደ ፈጸመለት አይታችኋል፤ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች፡**

1. ስለ ትዕሥት የምትማረው ምንድነው?
2. መከራን ተቀብለው ነገር ግን በሥጋ ያልተባረኩ ነቢያት የትኞቹ ናቸው? (ለምሳሌ፡- ሙሴ በምድረ በዳ ለ40 ዓመት ተንከራትቷል ነገር ግን ወደ ተስፋይቱ ምድር አልገባም፡፡)
3. በቁ.11 መሠረት ብፁዓን የሆኑት የትኞቹ ናቸው?
4. በያዕቆ፡5፡7 ላይ ባለው ክፍል ሐዋሪያው ያዕቆብ፡- ‹‹እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ታገሡ›› ይላል፡፡ ተስፋችን ምንድነው? ይህ ለአማኞች የተሰጠ ትዕዛዝ ነው፡፡
5. ለአንዳንድ ሰዎች ተስፋቸው በሰማይ እንጂ በምድር አይደለም፡፡ ለአንዳንዶቹ እንደ ኢዮብ ላሉ እግዚአብሔር በምድር እያሉ ሕይወታቸውን እንደገና ሊባርክ ይችላል:: እነዚህን ሁለት የተለያዩ ነገሮችን ስንመለከት አመለካከታችን እንዴት መሆን አለበት?
6. መከራን በተመለከተ ግልጽ ያልሆኑ (የምታነሣቸው ጥያቄዎች) ምንድናቸው? እነዚህን ጥያቄዎች አሁን ጻፋቸው፡፡ ከቡድንህ አባላት ጋር ተወያይተህ መልስ ማግኘት ትችላለህ፡፡
7. በቤተክርስቲያንህ ወይም በማህበረሰብህ ውስጥ መከራን በተመለከተ (አንድ ሰው እየተሰቃየ ቢያዩ) ሰዎች የሚሉአቸው (የሚያስቡአቸው) የተለመዱ ሀሳቦች ምንድናቸው? እነዚህ ሀሳቦች እውነት ናቸው ወይስ ሐሰት? ለምሳሌ፡ - አንዳንድ ሰዎች በሕይወታቸው መከራ ቢደርስባቸው በምድር ላይ ሳሉ እንደገና እንደሚበለጽጉ አንዳንድ ነቢያት ይናገሩላቸዋል::

## ትምህርት-5

ደረጃ-1

**መግቢያውን አንብብ፡-** እግዚአብሔር መልካም አምላክ ነው፡፡ ነገር ግን ዓለሙ የተበላሸ ስለሆነ ሐጢአት በሰዎች ሕይወት ላይ መከራን ያመጣል፡፡ ሰይጣን የክፋት ሁሉ ምንጭ ነው፡- ‹‹ሐጢአትን የሚያደርግ ሁሉ ከዲያብሎስ ነው፤ዲያብሎስ

ከመጀመሪያ ሐጢአት ሐጢአትን ያደርጋልና፡፡ ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ፡፡›› 1ዮሐ፡3፡8-9፡፡ እግዚአብሔር ለክፋት የሚሰጠው ምላሽ ኢየሱስን ነው፡፡ እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ተቆጣጣሪ ሲሆን አንድ ቀን ክፋትን ሙሉ በሙሉ እንደሚያጠፋ አቅዷል፡፡ ይህ ጊዜ እስኪደርስ እኛ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል አንዲት መከራ ስለ ደረሰባት ቤተክርስቲያን በሚቀጥለው ታሪክ አንብብ፡፡

ደረጃ-2

2ተሰ፡1፡3-10 ያለውን ክፍል አንብብ፡፡ ይህ ክፍል ከዚህ በታች ቀርቦልሃል፡፡ ‹‹እናንተ፣የእናንተ›› የሚሉ ስለ ተሰሎንቄ ሰዎች የሚናገሩትን ቃላት ተመልከት፡፡ እነዚህን ቃላት ከሥር አስምርባቸው፡፡ ይህን ክፍል ስታነብ እነዚህ ቃላት ያሉበትን ሥፍራ ስትደርስ አባላት በሙሉ እነዚህ ቃላት ያሉበትን ሥፍራ እንዲያውቁ አንድ ላይ ጮክ ብለው እንዲያነቡ አድርግ፡፡

| ሕዝብ፡ | እግዚአብሔር |
|---|---|

ወንድሞች ሆይ እምነታችሁ እጅግ ስለሚያድግ የሁላችሁም የእያንዳንዳችሁ ፍቅር እርስ በርሳችሁ ስለሚበዛ ሁል ጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን እንደሚገባ ልናመሰግን ግድ አለብን ስለዚህ በምትታገሱበት በስደታችሁና በመከራችሁ ሁሉ ከመጽናታችሁና ከእምነታችሁ የተነሣ በእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ስለ እናንተ ራሳችን እንመካለን፡፡
ስለ እርሱ ደግሞ መከራ ለምትቀበሉት ለእግዚአብሔር መንግሥት የምትበቁ ሆናችሁ ትቆጠሩ ዘንድ ይህ የእግዚአብሔርቅን ፍርድ ምልክት ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ከሥልጣኑ መላእክት ጋር ከሰማይ በእሳት ነበልባል ሲገለጥ መከራን ለሚያሳዩአችሁ መከራን መከራንም ለምትቀበሉ ከእኛ ጋር ዕረፍትን ብድራት አድርጎ እንዲመልስ በእግዚአብሔር ፊት በእርግጥ ጽድቅ ነውና፡፡ እግዚአብሔርን የማያቁትን ለጌታችንም ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል፡፡ በዚያም ቀን በቅዱሳኑ ሊከብር ምስክርነታችንንም አምናችኊልና በሚያምኑት ሁሉ ዘንድ ሊገረም ሲመጣ ከጌታ ፊት ከኃይሉም ክብር ርቀው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ፡፡

ደረጃ-3

አሁን ክፍሉን እንደገና አንብብና፡- እግዚአብሔር፣ኢየሱስ፣እርሱ፣ጌታ እና የእርሱ የሚሉትን ቃላቶች ፈልግና አክብባቸው፡፡

ደረጃ-4

## የውይይት ሀሳቦች፡

1. ያከበብካቸውን ቃላት እንደገና ተመልከትና ስለ ተሰሎንቄ ሰዎች የምትማሪውን በዝርዝር አስቀምጥ፡፡ የዘረዘርካቸውን ነገሮች በላይ በኩል ጥቅሱ በተጻፈበት ጎን በስተ

ግራ በኩል **ሕዝብ በሚለው ቃል ሥር** ጻፍ። ለምሳሌ፡- ‹‹ወንድሞችና እና አማኞች›› የሚሉትን ቃላት መጻፍ ትችላለህ።

2. በገጹ በስተቀኝ በኩል **እግዚአብሔር** በሚለው ቃል ሥር ስለ እግዚአብሔር የተማርካቸውን ነገሮች ዘርዝር። ለምሳሌ፡- እግዚአብሔር በሚለው ርዕስ ሥር ‹‹የእግዚአብሔር አብያተክርስቲያናት፣የእግዚአብሔር መንግሥት›› የሚሉትን መጻፍ ትችላለህ።
3. ከእነዚህ በሁለት ቦታ ከዘረዘርካቸው ነገሮች የምትማረውን ነገር ከቡድንህ አባላት ጋር ተወያይ?
4. በተሰሎንቄ ሰዎች ሕይወት እየሆነ ያለው ነገር ምንድነው? እነርሱ ለእምነታቸው የሰጡት ምላሽ ምንድነው?
5. በቁ.4 ላይ እንደተጠቀሰው መጽናት ማለት በመከራ ሁሉ መታገስ ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች ሳያወላውሉ መጽናትና መታገስ ይችሉ ዘንድ ብርታትን የሰጣቸው ማነው?
6. በቁ.7 መሠረት እግዚአብሔር ዕረፍትን የሚሰጠው መቼ ነው?
7. አንተ ሁል ጊዜ የምትጋደለው ከምን ጋር ነው? ለዚህ መጋደል በየጊዜው የምትሰጠው ምላሽ የተሰሎንቄ ሰዎች ከሰጡት ጋር እንዴት ሊነጻጸር ይችላል?

ደረጃ-5

ፍልጵ፡1፡29-30 እና 2ጢሞ፡3፡12 ያሉትን ክፍሎች አንብብ። ክፍሉ ከዚህ በታች ተጽፏል። እናንተ ወይም አማኞች የሚለውን ቃል ፈልግና ከሥሩ አስምርባቸው። ‹‹መከራ፣መጋደል እና ይሰደዳሉ›› በሚሉ ቁልፍ ቃላት ዙሪያ የሳጥን ምልክት ሳል።

ፍልጵ፡1፡29-30
‹‹ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና፤ ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም፤ በእኔ ያያችሁት አሁንም በእኔ እንዳለ የምትሰሙት ያው መጋደል ደርሶባችኋልና።››

ደረጃ-6

**የውይይት ጥያቄዎች፡**
1. በዚህ ክፍል መከራ የሚቀበለው ማነው? ለምን?
2. በቁ.29 ላይ ‹ተሰጥቶአችኋልና› የሚለው ቃል ስጦታ መስጠት ወይም ደግነትን ማሳየት ማለት ነው። ይህ ‹ተሰጥቶአችኋል› የሚለው ግሥ (ድርጊት) ፀጋ የሚለውን ቃል ይወክላል። ስለዚህ መከራ ስጦታ ወይም ጥሩ አጋጣሚ ነው! የፀጋን ቅርጽ የያዘ ቃል ነው።
3. ዛሬ ስለ አማኞችና እነርሱ በሕይወታቸው ስለሚደርስባቸው ነገር የተማርከው ምንድነው?

## ትምህርት-6

ደረጃ-1

**መግቢያውን አንብብ፡-** በአፍሪካ ውስጥ አንዳንድ ታዋቂ መንፈሳዊ አስተማሪዎች ክርስቲያኖች እንደማይታመሙ፤ድህነትም እንደማያውቃቸውና ችግር እንደማይደርስባቸው ያስተምራሉ። በእውነቱ የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረው ይህንኑን ነው? በባለፈው ትምህርት እንደተማርነው እውነት ከሆነ እኛ ሁላችን በትግልና በስቃይ ጊዜ ውስጥ ነው የምንኖረው። እንደ ናይጄሪያ ባሉ አገሮች ክርስቲያኖች በብዙ ቦታዎች አመጽ ይደርስባቸዋል። የተሰሎንቄ ሰዎች ጌታን ስለተቀበሉ ብዙ መከራ ይደርስባቸው ነበር። ይህ መከራ ሲደርስባቸው ከእምነታቸው ወደ ኋላ አላፈገፈጉም፤ይልቁን በመከራቸው ጸንተው እንዲቆሙ እግዚአብሔር እንዲረዳቸው በእግዚአብሔር ታመኑ። በዚህ ሳምንት ትምህርታችን ስለ ሐዋሪያው ጳውሎስ ሕይወትና በእርሱ ላይ ለደረሰበት መከራ የሰጠውን ምላሽ እንማራለን።

ደረጃ-2

ሐዋ፡13፡42-45 እና 49-50 ያሉትን ክፍሎች አንብብ። <u>አይሁድን</u> የሚያመለክቱትን ቃላት <u>ከሥር አስምርባቸው።</u>

ቁ.42 ጳውሎስና በርናባስ ለመሄድ በወጡ ጊዜ ይህን ነገር በሚመጣው ሰንበት ይነግሩአቸው ዘንድ ለመኑአቸው። ቁ.43 ጉባኤውም ከተፈታ በኋላ ከአይሁድና ወደ ይሁዲነት ገብተው ከሚያመልኩ ብዙዎች ጳውሎስንና በርናባስን ተከተሉአቸው፤ እነርሱም ሲነግሩአቸው በእግዚአብሔር ጸጋ ጸንተው እንዲኖሩ አስረዱአቸው። ቁ.44 በሁለተኛውም ሰንበት ከጥቂቶቹ በቀር የከተማው ሰው ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰሙ ዘንድ ተሰበሰቡ።
ቁ.45 አይሁድም ብዙ ሕዝብ ባዩ ጊዜ ቅንዓት ሞላባቸው፤እየተሳደቡም ጳውሎስ የተናገረውን ቃል ተቃወሙ።
ቁ.49 የጌታም ቃል በአገሩ ሁሉ ተስፋፋ። ቁ.50 አይሁድ ግን የሚያመልኩትን የከበሩትንም ሴቶችና የከተማውን መኳንንት አወኩ፤በጳውሎስና በበርናባስም ላይ ስደትን አስነሥተው ከአገራቸው አወጡአቸው።

ደረጃ-3

የውይይት ጥያቄዎች

1. ጳውሎስና በርናባስ ምን ያደርጉ ነበር?
2. ከአይሁድ ወገን የተወሰኑቱ ምላሽ የሰጡት በምን ዓይነት መንገድ ነበር? (ቁ.43 እና ቁ.45፣49)
3. በሐዋሪያው ጳውሎስና በበርናባስ ሕይወት መከራ የደረሰው እንዴት ነበር?
4. ለወንጌል ስትል መከራን የተቀበልክበትን ጊዜ ለቡድንህ አባላት ግለጽ።

ደረጃ-4

2ጢሞ፡3፡10-12 ያለውን ክፍል አንብብና ስደት፣ መከራ የሚሉትን ቃላት ሥር ወጣ ገባ በሆነ (ቀጥ ያላለ) መሥመር ምልክት አድርግባቸው።
2ጢሞ፡3፡10 አንተ ግን ትምህርቴንና አካሄዴን አሳቤንም እምነቴንም ትዕግሥቴንም ፍቅሬንም መጽናቴንም ስደቴንም መከራዬንም ተከተልህ፤ቁ.11 በአንጾኪያና በኢቆንዮን በልስጥራንም የሆነብኝን የታገሥሁትንም ስደት ታውቃለህ፤ጌታም ከሁሉ አዳነኝ። ቁ.12

በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ፡፡

ደረጃ-5

የውይይት ጥያቄዎች

1. አሁን ምልክት ያደረክባቸውን ቃላት ተመልከት፡፡ ስለ ጳውሎስ ሕይወት የምትማረው ምንድነው?
2. ቁ.12ን እንደገና አንብብ፡፡ ‹ሁሉ› የሚለውን ቃል አክብብ፡፡ ‹እግዚአብሔርን እየመሰሉ› እና ‹ሁሉ› የሚሉትን ቃላት በሳጥን ምልክት ውስጥ አስቀምጥ፡፡ ከዚህ የምትማረው ምንድነው?
3. ከጳውሎስ ምሳሌ መማር የምንችለው ምንድነው?

ደረጃ-6

2ቆሮ፡12፡7-10 ያለውን ክፍል አንብብ፡፡ ስለ ጳውሎስ የሚጠቅሱ ቃላትን ከሥር አስምርባቸው፡፡

<u>ሐዋሪያው ጳውሎስ</u>

2ቆሮ፡12፡7 ስለዚህም በመገለጥ ታላቅነት እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ እርሱም የሚጎስመኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ ይኸውም እንዳልታበይ ነው፡፡ ቁ.8 ስለዚህ ነገር ከእኔ እንዲለይ ሦስት ጊዜ ጌታን ለመንሁ፡፡ ቁ.9 እርሱም፡- ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ፡፡ እንግዲሕ የክርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ፡፡ ቁ.10 ስለዚህ ስለ ክርስቶስ በድካም በመንገላታትም በችግርም በስደትም በጭንቀትም ደስ ይለኛል፤ ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝና፡፡

ደረጃ-7

2ቆሮ፡12፡9-10 ያለውን ክፍል እንደገና አንብብና እርስ በራሳቸው የሚቃረኑትን ቃላት ፈልግ፡ ለምሳሌ፡- ‹ድካም እና ሃይል› እነዚህን ቃላት ፈልግና አክብባቸው፡፡

ደረጃ-8

የውይይት ጥያቄዎች

1. ከላይ ስለ ሐዋሪያው ጳውሎስ ያከበብካቸውን ቃላት ተመልከት፡፡ ስለ ሐዋሪያው ጳውሎስ ሕይወት የምትማራቸውን ነገሮች ከላይ በተጻፈው ጥቅስ ጎን ቀለል አድርገህ ዘርዝር፡፡
2. ስለ ድካምና ሃይል የሚያመለክቱን ቃላት ስትመለከት የምትማረው ነገር ምንድነው?
3. ከሐዋሪያው ጳውሎስ ምሳሌ ዛሬ የተማርከው ነገር ምንድነው?

4. በሕይወትህ መከራ ደርሶብህ ያውቃል? መቼ እንደደረሰብህና እግዚአብሔር በዚህ መከራ ጽናትንና ፀጋን የሰጠህበትን ጊዜ ለቡድንህ አባላት አካፍል፡፡

## ትምህርት-7

**ደረጃ-1**

**መግቢያውን አንብብ፡-** ሐዋሪያው ጳውሎስ እንዴት መከራን እንደተቀበለ በባለፈው ትምህርት ተምረን ነበር፡፡ እርሱ በእግዚአብሔር ላይ ከነበረው እምነት የተነሣ ድካሙን ሁሉ ለማሸነፍ የሚያስችል ታላቅ ሃይል ከእግዚአብሔር እንደተቀበለ ተምረን ነበር፡፡ እኛም ዛሬ ከአቅማችን በላይ በሆነው ነገር ሁሉ ላይ ታላቅ ሃይልን ከእግዚአብሔር መቀበል እንችላለን፡፡ ዛሬ የጌታችንን ኢየሱስ ምሳሌ እንመለከታለን፡፡ 1ጴጥ፡2፡18-25 ያለውን ክፍል አንብብና ‹የእናንተ ወይም እናንተ› ወዘተ

የሚሉትን ቃላት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያመልክቱትን ቃላት ከሥር አስምርባቸው፡፡ ‹መከራ› በሚለው ቃል ሥር ወጣ ገባ ወይም ቀጥ ያላለ መሥመር አድርግ፡፡ ከዚህ ክፍል የምትማረውን ነገር ‹መከራ› የሚለውን ቃል በያዘው ሳጥን ሥር ጻፍ፡፡

*መከራ*

ቁ.18 ሎሌዎች ሆይ ለበጎዎችና ለገሮች ጌቶቻሁ ብቻ ሳይሆን ለጠማሞች ደግሞ በፍርሃት ሁሉ ተገዙ፡፡ ቁ.19 በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ኃዘንን ቢታገሥ ምስጋና ይገባዋልና፡፡ ቁ.20 ኀጢአት አድርጋችሁ ስትጎሰሙ ብትታገሱ ምን ክብር አለበት? ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ስተቀበሉ ብትታገሡ ይህ ነገር በእግዚአብር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል፡፡ ቁ.21 የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንደትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ አናንተ መከራን ተቀብሎአልና፡፡

ቁ.22 እርሱም ኃጢት አላደረገም ተንኮልም በአፉ አልተገኘበትም፡፡ ቁ.23 ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፡፡ ቁ.24 ለኃጢት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር ‹‹እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ›› ቁ.25 በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ፡፡ እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኂል፡፡

ደረጃ-2

1ጴጥ፡2፡18-25 ያለውን ክፍል እንደገና አንብብና ስለ ኢየሱስ በሚናገሩ ቃላት ላይ የመስቀል ምልክት አድርግ፡፡ በቁ.19 እና 20 ላይ ‹ምስጋና ይገባዋል› የሚለውን ቃል አክብብ፡፡ የዚህ ቃል ትርጉም ምንድነው?

ደረጃ-3

የውይይት ጥያቄዎች

1. በመከራ ላይ እኛ መስጠት የሚገባንን ምላሾች ጻፍ፡፡ ለምሳሌ፡- ለገዢዎቻችን መታዘዝ እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡ ይህ መታዘዝ የሚለው ቃል ክርክርን ሊያስነሣ ይችላል፤ነገር ግን ኢየሱስ ምሳሌውን በተጠቀመበት አውድ (context) ላይ ትኩረት አድርግ፡፡ ይህ መከራ ወይም እርስ በርስ አለመስማማት ሲፈጠር የምናደርገው ውይይት ነው፡፡
2. እኛ የምንከተለው የማን ምሳሌ ነው? ከላይ በክፍሉ ውስጥ የመስቀል ምልክት ያደረክባቸውን ቃላት ተመልከት፡፡ በመከራና በስድብ ላይ ምላሽ ለመስጠት ኢየሱስ ያደረገውን ነገር ጻፍ፡፡
3. ‹ምስጋና ይገባዋል› ማለት አንድ ሰው ለሠራው መልካም ሥራ ምስጋናን ይቀበላል ማለት ነው፡፡ በቁ.19 እና 20 መሠረት አንተ ከእግዚአብሔር ምስጋናን መቀበል የምትችለው መቼ ነው?
4. በቁ.21 መሠረት እኛ የተጠራንለት ዓላማ ምንድነው?
5. አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች ሲበደሉ ምላሽ የሚሰጡት እንዴት ባለ መንገድ ነው?
6. ዛሬ የተማርከው እውነት ምንድነው?

ደረጃ-4

ዕብ፡5፡7-8 አንብብና ስለ ኢየሱስ በሚናገሩ ቃላት ላይ የመስቀል ምልክት አድርግ፡፡

ቁ.7 እርሱም በስጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፡፡ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት፤ ቁ.8 ምንም ልጅ ቢሆን ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፡፡

የውይይት ጥያቄዎች፡

1. ስለ ኢየሱስ የምትማረው ምንድነው?
2. አንድ ሰው ቢበድልህ ትፀልይለታለህ ወይስ ትበቀለዋለህ?
3. ከመከራችን መማር የምንችለው ምንድነው? መከራ በሕይወትህ ላይ ለውጥ አምጥቷልን?

## ትምህርት-8

ደረጃ-1

**መግቢያውን አንብብ፡-** ክርስቶስ የኑሮአችን ምሳሌ ነው፡፡ እኛ የክርስቶስ ተከታዮች እንደመሆናችን መጠን በኑሮአችን እርሱን ለመምሰል እንሻለን፡፡ እርሱ ለአባቱ ፈቃድ ራሱን አስገዝቶ ስለ እኛ መከራን ተቀብሏል፡፡ ሐዋሪያው ጴጥሮስ ሲናገር፡- ‹‹ወዳጆች ሆይ በእናንተ መካከል እንደ እሳት ሊፈትናችሁ ስለሚሆነው መከራ ድንቅ ነገር እንደ መጣባችሁ አትደነቁ፡፡›› መከራ በሕይወታችን ቢመጣ ለመጋፈጥ ዝግጁዎች መሆን ያስፈልገናል እንጂ መደነቅ የለብንም፡፡

ደረጃ-2

1ጴጥ፡4፡1-2 እና ቁ.12-16 እና ቁ.19 ያለውን ክፍል አንብብና መከራ በሚለው ቃል ሥር አስምርበት፡፡

ቁ.1 ክርስቶስም በሥጋ ስለ እኛ መከራን ስለተቀበለ ከእንግዲህ ወዲህ በሥጋ ልትኖሩ በቀረላችሁ ዘመን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ እንደ ሰው ምኞት እንዳትኖሩ እናንተ ደግሞ ያን አሳብ እንደ ዕቃ ጦር አድርጋችሁ ያዙት፤ በሥጋ መከራን የተቀበለ ኃጢአትን ትቶአልና፡፡
ቁ.12 ወዳቾች ሆይ በእናንተ መካከል እንደ እሳት ሊፈትናችሁ ስለሚሆነው መከራ ድንቅ ነገር እንደ መጣባችሁ አትደነቁ፤ ቁ.13 ነገር ግን ክብሩ ሲገለጥ ደግሞ ሐሤት እያደረጋችሁ ደስ እንዲላችሁ በክርስቶስ መከራ በምትካፈሉበት ልክ ደስ ይበላችሁ፡፡ ቁ.14 ስለ ክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ፡፡ ቁ.15 ከእናንተ ማንም ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም ክፉ አድራጊ እንደሚሆን ወይም በሌሎች ጉዳይ እንደሚገባ ሆኖ መከራን አይቀበል፤ ቁ.16 ክርስቲያን እንደሚሆን ግን መከራን ቢቀበል ስለዚህ ስም እግዚአብሔርን ያመስግን እንጂ አይፈር፡፡ ቁ.19 ስለዚህ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መከራን የሚቀበሉ መልካምን እያደረጉ ነፍሳቸውን ለታመነ ፈጣሪ አደራ ይስጡ፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች፡**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ መከራ የሚለው ቃል በክፍሉ ውስጥ በእያንዳንዱ ቦታ እንዴት እንደተገለጸ ተመልከት፡፡

1. ስለ መከራ የምትማረው ምንድነው? በአንተ ሕይወት መከራ ሊመጣ የሚችልባቸው ጥቂት ምክንያቶች ምንድናቸው?
2. እኛ መኖር ያለብን ለምንድነው? ቁ.2
3. ለመከራ ያለን አመለካከት ምን መሆን አለበት?
4. ከመከራ የምናገኘው ጥቅም ምንድነው?
5. ዛሬ የተማርከውን እውነት ጠቅለል አድርገህ ተናገር፡፡ እያንዳንዱ የቡድኑ አባል አንድ የማጠቃለያ ሀሳብ ለቡድኑ አባላት ማካፈል አለበት፡፡
6. ወደ ፊት በሕይወትህ መከራ ቢደርስብህ መቋቋም እንድትችል ዛሬ በሕይወትህ መምጣት የሚያስፈልጋቸው ለውጦች ምንድናቸው?

## ትምህርት-9

ደረጃ-1

**መግቢያውን አንብብ፡-** በሕይወታችን መከራና ስቃይ ሲደርስብን እግዚአብሔር ዝም የሚለው ለምን እንደሆነ መረዳት ያዳግተናል፡፡ በብሉይ ኪዳን ኢዮብ የሚባል ሰው ቤተሰቡንና ሀብቱን በሙሉ እስኪያጣ ድረስ ስቃይ ደርሶበታል፡፡ እዮብ ለሥቃዩ ምንም ዓይነት ምላሽ ከእግዚአብሔር አላገኘም፡፡ ይሁን እንጂ ቃሉን በማንበብ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ዓላማዎቹን (ለምሳሌ፡- በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድናድግ ማድረግ) ማየት እንጀምራለን፡፡

ደረጃ-2

2ቆሮ፡4፡7-11 ያለውን ክፍል አንብብና ስለ ሐዋሪያው ጳውሎስ የሚናገሩትን ቃላቶች ከሥር አስምርባቸው፡፡ በክፍሉ ውስጥ በተከታታይ እርስ በርስ የሚቃረኑ ሀሳቦችን ፈልግ፡፡ ‹‹ነገር ግን›› የሚለውን ቃልና ‹‹እንጂ›› የሚለውን ቃል በሳጥን

ምልክት ውስጥ አስቀምጥ፡፡ ‹‹እንዳይሆን›› እና ‹‹ይገለጥ ዘንድ›› የሚሉትን ቃላት አክብብ፡፡

ቁ.7 ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን፤ ቁ.8 በሁሉ እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም፤ እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም፤ ቁ.9 እንሰደዳለን እንጂ አንጣልም፤ እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም፤ ቁ.10 የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁል ጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞራለን፡፡ ቁ.11 የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሚሞት ሥጋችን ይገለጥ ዘንድ እኛ ሕያዋን የሆንን ከኢየሱስ የተነሣ ዘውትር ለሞት አልፈን እንሰጣለንና፡፡

ደረጃ-3

የውይይት ጥያቄዎች፡

1. ስለ ሐዋሪያው ጳውሎስና ስለ ወዳጆቹ ከዚህ ክፍል የምትማረው ምንድነው? ችግሮቻቸውን ዘርዝር፡፡
2. በሕይወታቸው መከራ የደረሰው ለምንድነው?
3. ‹‹እንጂ›› በሚለው ቃል የተያያዙትን ዓ.ነገሮች በዝርዝር አስቀምጥ፡፡ ለምሳሌ፡- ‹‹እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም፡፡››
4. ስለ ሐዋሪያው ጳውሎስ እምነትና እርሱ ለመከራ ስለሰጠው ምላሽ የምትማረው ምንድነው?
5. ‹‹እንዳይሆን›› እና ‹‹ይገለጥ ዘንድ›› የሚሉትን ቃላት ተመልከት፡፡ ይህ መከራ በእነርሱ ላይ እንዲደርስ እግዚአብሔር የፈቀደው ለምንድነው? በሚደርስባቸው መከራ ላይ የእግዚአብሔር ዓላማ ምንድነው?

ደረጃ-4

1ጴጥ፡1፡6-7 ያለውን ክፍል አንብብና ‹‹እናንተ›› የሚለውን ቃል የሚያመለክቱትን ሀሳቦች ከሥር አስምርባቸው፡፡ ‹‹ዘንድ›› የሚለውን ቃል በሳጥን ምልክት ውስጥ አስቀምጥ፡፡ ከዚህ የምትማረው ምንድነው?

ቁ.6 እና 7 በዚህም እጅግ ደስ ይላችኋል ነገር ግን በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ የሚከብር የተፈተነ እምነታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ ለምስጋናና ለክብር ለውዳሴም ይገኝ ዘንድ አሁን ለጠቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል፡፡

ደረጃ-5

ሮሜ፡5፡1-5 ያለውን ክፍል አንብብና ‹‹እኛነታችንን›› በሚያሳዩ ቃላት ከሥር አስምርባቸው፡፡ ከዚህ የምትማረውን ነገር በስተግራ በኩል ባለው ክፍት ቦታ ዘርዝር፡፡ ‹‹ስለ›› የሚለውን ቃል በሳጥን ምልክት ውስጥ አስቀምጥ፡፡

ቁ.1 እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፤ ቁ.2 በእርሱም ደግሞ ወደ ቆምንበት በደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል፤ በእግዚአብሔር ክብርም ተስፋ እንመካለን፡፡ ቁ.3 እና 4 ይህም ብቻ

አይደለም፤ ነገር ግን መከራ ትዕግሥትን እንዲያደርግ ትዕግሥትም ፈተናን ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ እያወቅን በከራችን ደግሞ እመካለን ቁ.5 በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም፡፡

ደረጃ-6

የውይይት ጥያቄዎች

1. ሐዋሪያው ጳውሎስ የሚመካው በምንድነው?
2. ሐዋሪያው ጳውሎስ በመከራ የሚመካው ለምንድነው? መከራ የሚያመጣው ውጤት ምንድነው?
3. በቁ.3-5 የተዘረዘሩትን ደረጃዎች ተወያዩ፡፡ (መከራ፣ትዕግሥት፣ፈተና፣ተስፋ) እነዚህ ነገሮች አንደኛው ለሌላኛው ውጤት የሆነው ለምንድነው? እግዚአብሔር ወደ መንፈሳዊ ብስለት እየመራ ነው፡፡
4. እነዚህ መንፈሳዊ ብስለትና የእግዚአብሔር ፍቅር እውኔታዎች በመከራ ሰዓት እንዴት ያጽናኑሃል?

**አስተያየት**፡- እግዚአብሔር መከራን የሚጠቀመው እኛ እንድንለወጥ ነው፡፡ እኛ መከራ አንወድም፡፡ ይሁን እንጂ መከራ እኛን ያነጻናል፤ እግዚአብሔርም በእኛ ውስጥ እንዳለ ለሌሎች እንድናሳይ ያደርጋል፡፡ ለመከራ የምንሰጠው ምላሽ ለእግዚአብሔር ክብርን የሚያመጣ መሆን አለበት፡፡ መዝ፡(66)፡10፡-‹‹አቤቱ ፈትነኸኛልና ብርንም እንደሚያነጠሩት አንጥረኸኛልና›› ይላል፡፡ የብር አንጥረኛ ብሩን በእሳት እንዲግል ያደርገዋል፡፡ ንጹሕ ያልሆኑ ክፍሎች ወደ ላይ ይወጣሉ፤አንጥረኛውም ያስወግዳቸዋል፡፡ ይህ ሂደት ብሩ ሙሉ በሙሉ ንጹሕ እስኪሆን ድረስ ይቀጥላል፡፡ ሙሉ በሙሉ ንጽሕ ሲሆን እንደ መስታወት ይሆናል፤አንጥረኛውም እንደ መስታወት በሚያሳየው ብር ራሱን ማየት ይችላል፡፡ እግዚአብሔር እንደዚሁ ልጆቹ ንጹሕ እንዲሆኑና እንደመስታወት እርሱን እንዲያሳዩት በ‹እሳት› ያጠራቸዋል፡፡

## ትምህርት-10

ደረጃ-1

***መግቢያውን አንብብ፡-*** *መከራ የእግዚአብሔርን ባሕሪይና ፀጋ ለማሳየት ጥሩ እድል እንደሚፈጥር በባለፈው ትምህርት ተምረን ነበር፡፡ አንድ አማኝ፡- ‹‹በሕይወቴ መከራ የሚደርሰው ለምንድነው ብሎ ከመጠየቅ መከራን እንደመልካም ነገር ቆጥሮ መከራ ቢመጣብኝ እንዴት ሳልፈራ በጽናት ማለፍ እችላለሁ ወይም እየደረሰብኝ ካለው መከራ ምን መማር እችላለሁ ብሎ ራሱን መጠየቅ አለበት፡፡ እኛ ከሚደርስብን መከራ ተምረን ሌሎች በመከራ ውስጥ የሚያልፉትን እንድናጽናና እግዚአብሔር ይህንን የመከራ ጊዜ ለመልካም ሊጠቀም ይችላል፡፡ በመከራ ጊዜ የሚያጽናናን የእግዚአብሔር ቃል እውነት ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡*

ደረጃ-2

ሮሜ፡8፡35-39 ያለውን ክፍል አንብብና እኛን ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለዩን የማይችሉን ነገሮች ፈልግ፡፡ ከእያንዳንዱ ቃል በላይ ቁጥር ጻፍ፡፡

ቁ.35 ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ወይስ ጭንቀት ወይስ ስደት ወይስ ራብ ወይስ ራቁትነት ወይስ ፍርሃት ወይስ ሰይፍ ነውን? ቁ.36 ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንጋደላለን እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደተጻፈ ነው። ቁ.37 በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን። ቁ.38 ሞት ቢሆን ሕይወትም ቢሆን መላእክትም ቢሆኑ ግዛትም ቢሆን ያለውም ቢሆን የሚመጣውም ቢሆን ኃይላትን ቢሆኑ ቁ.39 ከፍታም ቢሆን ዝቅታም ቢሆን ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።

**የውይይት ጥያቄዎች፡**

1. እግዚአብሔር እንደሚወድህ ታምናለህ? እግዚአብሔር አይወደኝም ብለህ ተጠራጥረህ ታውቃለህ? ካለ ያን ጊዜ ብትገልጽ? እንድትጠራጠር ያደረገህ ምንድነው? ሮሜ፡8፡35-39 ያለው ክፍል በመከራ ጊዜ እንዴት እንደሚያጽናናህ ከቡድንህ አባላት ጋር ተወያዩ።

ደረጃ-3

2ተሰ፡1፡5-10 ያለውን ክፍል አንብብና ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለሚጽፍላቸው ሰዎች የሚገልጹትን ቃላት ከሥር አስምር። ለምሳሌ፡- ‹‹ለምትቀበሉት---››።

ቁ.5 ስለ እርሱ ደግሞ መከራ ለምትቀበሉትሉት ለእግዚአብሔር መንግሥት የምትበቁ ሆናችሁ ትቆጠሩ ዘንድ ይህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ ምልክት ነው። ቁ.6-7 ጌታ ኢየሱስ ከሥልጣኑ መላእክት ጋር ከሰማይ በእሳት ነበልባል ሲገለጥ መከራን ለሚያሳዩአችሁ መከራን መከራንም ለምትቀበሉ ከእኛ ጋር እረፍትን ብድራት አድርጎ እንዲመልስ በእግዚአብሔር ፊት በእርግጥ ጽድቅ ነውና። ቁ.8 እግዚብሔርን የማያውቁትን ለጌታችንም ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል ቁ.9-10 በዚያም ቀን በቅዱሳኑ ሊከብር ምስክርነታችንንም አምናችኂልና በሚያምኑት ሁሉ ዘንድ ሊገረም ሲመጣ ከጌታ ፊት ከኃይሉም ክብር ርቀው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ።

ደረጃ-4

ክፍሉን እንደገና አንብብና አማኞችን ስለሚያስጨንቁ ሰዎች የሚገልጹትን ቃላት በሳጥን ምልክት ውስጥ አስቀምጥ። ለምሳሌ፡- ‹‹መከራን ለሚያሳዩአችሁ---›› ስለ ጊዜ የሚናገሩትን ቃላት ፈልግና አክብብ።

የውይይት ጥያቄዎች፡

1. አማኞችን መከራ ስለሚያሳዩአቸው ሰዎች የምትማረው ምንድነው አማኞችን መከራ የሚያሳዩአቸው ሰዎች ምን ይሆናሉ
2. ከዚህ ክፍል ስለ እግዚአብሔር የምትማረው ምንድነው
3. ከላይ ያከበብካቸውን ቃላት ተመልከት። አማኞች ከመከራቸው የሚያርፉት <u>መቼ</u> ነው አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በዚህ ምድርም ሳለን እረፍትን ሊሰጠን ይችላል።
4. እግዚአብሔር ለአንተ ያለው ፍቅሩ ምን ያህል ነው እርሱ እንደሚወድህ የሚሰጥህ ማረጋገጫ ምንድነው

5. ይህ እውነት በመከራ ጊዜ እንዴት ሊያጽናናህ ይችላል
6. በአንተ ላይ በደረሰው መከራ ትምህርት አግኝተህ ሌላውን እንድታጽናና እግዚአብሔር ያንን መከራ የተጠቀመበት ጊዜ ካለ ለቡድንህ አባላት አካፍል፡፡
7.

ደረጃ-5

1ጴጥ፡4፡19 ያለውን ክፍል በቃል አጥና፡- ስለዚህ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መከራን የሚቀበሉ መልካምን እያደረጉ ነፍሳቸውን ለታመነ ፈጣሪ አደራ ይስጡ፡፡